"የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን ... ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ታል እንድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን፡፡ ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፤ በበጎነትም እውቀትን፤ በእውቀትም ራስን መግዛት፤ ራስንም በመግዛት ጽናትን፤ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፤ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፤ በወንድማማች መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ"[182] እንደ ተባልን እውነተኛ ክርስቲያን በመሆን ክርስቶስን የምንመስልበትን ሕይወት መጀመርና ቀስ በቀስ እያሳደግን መሄድ ይኖርብናል፡፡

6.2.3. ትሕትና

ትሕትና አንድ ክርስቲያን ገንዘብ ሊያደርጋቸው ከሚገቡት ሥነ ምግባራት መካከል ዋናውና የክርስትና መገለጫው ነው፡፡ ትሕትና በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ቦታ ያለው የሁሉም ሥነ ምግባራት እናት፤ የፍቅር መሠረት፤ የፍጹምነት ማሠሪያ፤ የቁጣ መመለሻ፤ የነፍስን ጸጥታና ሰላም የምታሰጥ መንገድ ናት፡፡ እርሷም የመታዘዝ መሠረት፤ የፍጹምነት ጥበብ፤ በክርስትና ነፍስና አእምሮ የሚያበሩባት ጐዳና ናት፡፡

ትሕትና ሊወሰድና ሊሠረቅ የማይችል በጥበብ የተሞላ ሀብት፤ የሁሉም ሥነ ምግባር መግቢያ በር፤ የፍጹምነት ቁልፍ፤ የእርቅና የሰላም ማሠሪያ፤ የፍቅር መጠበቂያ፤ በጸጥታና በሥነ ምግባር የተሞላ መዝገብና የሁሉም ምግባራት ምንጭ ነው፡፡ ትሕትና ከሌሎች ምግባራት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ትሕትና የሌለው ሰው ሁሉንም ምግባራት ያጣል፤ ምክንያቱም ትሕትና የሁሉ ምግባራት

---

[182] 2ኛ ጴጥ. 1:3-8

መሠረት ናትና። ትሕትናን በተማርንና ባወቅን ቁጥር ነፍሳችን በምግባራት ትበለጽጋለች። ትሑት የሆነ ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዛትና ሕጐች ሁሉ ያለ ብዙ ድካምና መቸገር ለመጠበቅ ይቻለዋል። "የእግዚአብሔር ምሕረት ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ፥ ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ ነው። ቃል ኪዳኑን በሚጠብቁ፥ ትእዛዙንም ያደርጉት ዘንድ በሚያስቡ ላይ ነው።"[183] እንደ ተባለ።

ሰው ከአፈር መፈጠሩን መዘንጋት የለበትም፥ "ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፥ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና"[184] ያለውን ቃል ዘወትር ማሰብ አለበት። "ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና አቤቱ፥ እኛ አፈር እንደ ሆንን አስብ። ሰውስ ዘመኑ እንደ ሣር ነው፥ እንደ ዱር አበባ እንዲሁ ያብባል፥ ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ያልፋልና፥ ስፍራውንም ደግሞ አያውቀውምና"[185] እንደ ተባለ። ስለዚህ ሰው በዚህ ምድር ለዘለዓለም እንደማይኖር በመገንዘብ በትሑት ሰብእና ሰውን ሁሉ በመውደድና በማክበር ራሱን ዝቅ በማድረግ ያለ ትዕቢት ሊኖር ይገባዋል። ትዕቢት ለክርስቲያን አይስማማውምና።

ትሕትና ሰው እግዚአብሔርንና ባልንጀራውን በእውነት እንዲወድድና በሌሎች ደስታና የሕይወት ስኬት ያለ ምንም ቅንዓትና ምቀኝነት ስሜት ከልቡ የሚደሰት እንዲሆን ያደርገዋል። ትሕትና ያለው ሰው በሌሎች ሰዎች ውድቀት፥ የሕይወት መመሰቃቀልና ችግር አይደሰትም። ምክንያቱም ሰውን ሁሉ ከልቡ እንደ ራሱ ይወድዳል፥ ያከብራልና ነው። ትሕትና ያለው ክርስቲያን ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ከቲጣ የራቀ ሰላማዊና ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ስለሚሆን ከሁሉም ጋር በሰላም ይኖራል።

---

[183] መዝ. 102፥ 17
[184] ዘፍ 3:19

እግዚአብሔር ትዕቢትን ፈጽሞ ይጠላል፡ ትዕቢት ከእግዚአብሔር ይለያል። ትሕትና ግን ሥነ ምግባራት ሁሉ የሚገነቡባትና የሚጠበቁባት የመንፈሳዊ ፀጋዎች ሁሉ ምንጭና መሠረት ናት። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ ከተፈለገ መጀመሪያ ትሕትናን ገንዘብ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌል መሠረት የሆነውንና "የተራራው ስብከት" ተብሎ የሚታወቀውን ትምህርቱን ማስተማር በጀመረበት ጊዜ በመጀመሪያ ያስተማረው ስለ ትሕትና ነበር፡ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፡ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና"[186] በማለት። በመንፈስ ድህ መሆንና ልብን ንጹሕ ማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተሳስሩን ምግባራት ናቸው። "ልበ ንጹሐት ብፁዓን ናቸው፡ እግዚአብሔርን ያዩታልና።"[187]

ትሕትና የሌለበት ማንኛውም ዓይነት ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በክንቱ ውዳሴ ተጠልፎ በዲያብሎስ ለመወሰድ የተጋለጠ ነው። ምክንያቱም ትሕትና የሌለው ሰው ስለ ራሱ አድናቆትና ውዳሴ እንዲሁም ክብርና ዝና አጥብቆ የሚፈልግ ስለሚሆን ነው። በሰዎች ዘንድ አቤት እገሌ ትሕትናው ለመባል ለክንቱ ውዳሴ የይምሰል ሕይወት የምንኖር ከሆነም አስቸጋሪ ነው። ትሕትና ውጫዊ ጠባይ ብቻ አይደለም፡ ውሳጣዊ አመለካከትም ነው እንጂ። ይልቁንም እውነተኛ ትሕትና አፍአዊ ሳይሆን ከውስጥ ዘልቆ የሚወጣ ነው። ስለዚህ ጌታችንም በመጀመሪያ እንዳስተማረው ትሕትና የሁሉ ምግባራት ሁሉ እናት ስለ ሆነች ለአንድ ክርስቲያን የመጀመሪያው ምግባር ትሕትና መሆን እንዳለበት እንረዳለን። በእርሷ ሁሉንም ሥነ ምግባራት ገንዘብ እናደርግባታለንና።

---

[186] ማቴ. 5:3
[187] ማቴ 5:8

አንድ ሰው ከውስጥ ያይደለና የእውነት ያልሆነ፥ እንዲሁ ለታይታና ለይምሰል የሆነ ውጫዊ የማስመሰል ትሕትና የሚያሳይ ከሆነ ይህ ሰው በውስጡ ፊጽሞ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግና በልቡ ኃይለኛ ትዕቢት ያለበትና ለራሱ ክብርና ዝና የሚፈልግ ስለሚሆን የሚያደርገው ነገር ሁሉ ከንቱ ውዳሴን ለማግኘት ሲል ይሆናል። እንዲህ ያለ ሰው ሥራው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር የማያገናኘው ከንቱ ድካም ይሆንበታል፥ ምክንያቱም ክርስትና ከልብ እንጂ በውጫዊ ገጽታ ብቻ ተለጥፎ የሚታይ አይደለምና።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር ጸጋውንና በረከቱን አብዝቶ የሚያፈስስላቸውና ምስጢሩን የሚገልጥላቸው ትሑታን ለሆኑ ሰዎች ነው፥ ምክንያቱም እንዲህ ያሉት ሰዎች የሚሰጣቸውን ጸጋ ለመሸከም እንደሚችሉና እንደማይኰሩበት እርሱ ያውቃልና ነው። "ስለዚህ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል"[188] ፤ እንዲሁም "ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"[189] ተብሏልና ጸጋ እግዚአብሔርን እናገኝ ዘንድ ትሑታን ልንሆን ይገባናል። ትሑታን ሰዎች ትሕትናቸው እያደገ በሄደ ቁጥር በጸጋ ላይ ጸጋ፥ በክብር ላይ ክብር ይፈሠርላቸዋል፥ እነርሱ በእግዚአብሔር ፊት የበለጠ ነፍሳቸውን አፍስሰዋልና።

ስለ ትሕትና ለማወቅና ለመማር ወይም ትሕትናን ከማን እንማር? የምንል ከሆነ ትሕትናን የምንማረው ምሳሌውን ከተወልን ከባለቤቱ፥ ከመድኃኔ ዓለም ክርስቶስና እርሱን መስለው ካለፉት ቅዱሳን ነው። እርሱንም ከዚህ በታች በጥቂቱ እንመለከታለን።

---

[188] ያዕ. 4:6
[189] 1ኛ ጴጥ. 5:5

Scanned by CamScanner

6.2.3.1. ክርስቶስ ትሑት ነውና

"ከእኔ ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ"[190] እንዳለን ጌታችን፣ ክርስቲያን የክርስቶስ ተከታይ ስለ ሆነ አብነት የሚያደርገው "እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝ" ያለውን ክርስቶስን ነው፡፡ መምህራችንና አምላካችን እርሱ "ከእኔ ተማሩ" ብሎናልና፡፡ ክብርና ምስጋና ይግባውና እርሱ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሰው ሆኖ ሁሉንም ነገር አስተምሮናል፡፡ "እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፣ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም። ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ፣ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፣ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል[191] ጠልተውማል"[192] እንዳለ፡፡

መድኃኒታችን በዘመነ ሥጋዌው የሠራቸውን ሥራዎችና ያስተማረውን ትምህርት ልብ ብለን አስተውለን ልናይ ይገባል፡፡ ከልደቱ እስከ ዕርገቱ ድረስ ትሕትናን በሚገባ አሳይቶናል፡፡ ትሕትናውንም በተግባር ሲያሳየን ዘለዓለማዊ አምላክ ንጉሠ ሰማይ ወምድር የሆነ እርሱ በበረት ተወለደ፣ ወደ ግብጽ ተሰደደ፣ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀመጠ፣ "እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና"[193] በማለት የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ ስድብንና ነቀፋን ታግሦ ተቀበለ፡፡

---

190 ማቴ. 11:29

191 "እኔና አብ አንድ ነን" ዮሐ. 10:30 "እኔን ያየ አብን አይቷል" ዮሐ. 14:9

192 ዮሐ. 15:22-24

193 ማቴ. 13:14-17

Scanned by CamScanner

በመቀጠልም አብነት የምናደርጋቸው በሕይወታቸው መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው ያለፉትን ቅዱሳንን ነው።

6.2.3.2. ቅዱሳን ትሩታን ናቸውና

ቅዱሳን ብዙ ፈተናዎችን በአኩቴት የተቀበሉና ድል እያደረጉ ያለፉ፡ ብዙ ጸጋ እግዚአብሔርን ያገኙና በቅድስና መንገድ ብዙ ርቀት የተጓዙ ቢሆኑም እንኳ ሁል ጊዜ ራሳቸውን በትሕትና ዝቅ ያደርጋሉ። ንግግራቸውና አስተሳሰባቸው፡ አጠቃላይ ሕይወታቸው ሁሉ በትሕትና የታጀበ ነው። "ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፡ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል"[194] የሚለውን የጌታ ቃል ለሕይወታቸው መመሪያ በማድረግ በማስመሰል ያይደለ በእውነት፡ አፍአዊ ያይደለ ውሳጣዊ ትሕትናን በመላበስ የእውነት ሰዎች ሆነው በዚህ ምድር አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር አድርገው[195] በመጨረሻም ወደ እርሱ ሄደዋል።

"የዳዊት ልጅ፡ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ" ተብሎ በወንጌሉ መጀመሪያ ላይ ለተነገረው ለኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ መጀመሪያ ሆነው የተጠቀሱት፡ "እኔ የአብርሃም አምላክ፡ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ"[196] ብሎ የተናገረላቸው እነ አበ ብዙኃን አብርሃም እና "እንደ ልቤ"[197] ብሎ እግዚአብሔር የመሰከረለት ነቢዩ ዳዊት እንዴት ባለ ፍጹም ትሕትና እንደ ኖሩና በታላቅ ትሕትና ከእግዚአብሔር ፊት ይቀርቡ እንደ ነበር እናስታውስ። አብርሃምም እግዚአብሔር

---

[194] ማቴ. 23፡12

[195] "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፡...ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፡ እግዚአብሔር ወስዶታልና።" ዘፍ 5፡22-24

[196] ማቴ. 22፡31-32 ፡ ዘጸ 3፡6

[197] 1ኛ ሳሙ. 13፡14

Scanned by CamScanner

ሰዶምና ገሞራን እንዳያጠፋት እየማለደ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ አያለ ደጋግሞ የምልጃ ልመና ባቀረበ ጊዜ ትሕትናውን ሲገልጽ፡ "እኔ አፈርና አመድ ስሆን ከጌታዬ ጋር እናገር ዘንድ እነሆ አንድ ጊዜ ጀመርሁ" አለ።[198] ነቢዩ ዳዊትም የእሥራኤል ንጉሥ ሆኖ እያለ ነገር ግን ከትሕትና የተነሣ "እኔ ግን ትል ነኝ፡ ሰውም አይደለሁም፡ የሰው ማላገጫ በሕዝብም ዘንድ የተናቅሁ ነኝ" አለ።[199]

ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ጊዜ የተነጋገረው፡ ሕይወቱን በሙሉ በተልእኮና እግዚአብሔርን በማገልገል ያሳለፈው፡ እግዚአብሔር በተአምራት እሥራኤልን ባሕርን ከፍሎ ሲያሻግራቸውና ከግብጽ ሲያወጣቸው አርባ ዘመን በምድረ በዳ የመራቸውና ያስተዳደረው ነቢዩ ሙሴ "ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ"[200] ተብሎ ተነግሮለታል።

❖ ርእሰ መነኰሳት የሆነው ታላቁ ቅዱስ እንጦንስ ዲያብሎስ እርሱን ለማጥቃትና ለማወክ በመጣበት ጊዜ እንዲህ በማለት በትሕትና መለሰለት፡- "አንተ ብርቱ ነህ፡ ከእኔ ከደካማው ምን ፈለግህ? እኔ ከእናንተ ከአንዱ ጋር እንኳን መታገል የማልችል ነኝ። አቤቱ፡ አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔ ምናምንቱ አመድና ትቢያ ነኝና ከእነዚህ አድነኝ" በማለት በፍጹም ትሕትና ሲጸልይ ዲያብሎስ በሰማው ጊዜ እንደ ጢስ ተንኖ ጠፋ። ቅዱስ እንጦንስ በሚያስደንቅ ሁኔታ ትሕትናን ፍጹም ገንዘብ አድርጓልና፡[201] በሊሎች የቅዱሳን ሕይወትም ተመሳሳይ ነገር እናነባለን።

---

[198] ዘፍ. 18:27
[199] መዝ. 22:6
[200] ዘኍ. 12:3
[201] St. Athanasius, *The Life of St.*

❖ በታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ ሕይወትም እንዲሁ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይፈትነው የነበረውን ዲያብሎስን እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዴት በትሕትና ድል ይነሣው እንደ ነበር እንመለከታለን። ቅዱስ መቃርዮስን ያገለግለው የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ ኪሩብ፡ ራስን ከፍ ከማድረግ እንዲጠበቅ ሲመክረው፡ "በምታደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግን እንጂ ራስህን ከፍ ከፍ እንዳታደርግ ተጠበቅ" አለው። ቅዱስ መቃርዮስም "እነሆ ሰይጣናት ነፍስና ሥጋዬን እያስፈሩኝና እያሰቃዩኝ ምኑን እታበየዋለሁ፡ ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ረዳት የለኝም፡ ፈውስን የምታደርግልኝ ጸጋው ናትና" አለው። ለቅዱሳን ራስን ከፍ ከፍ ማድረግና ትዕቢት አይስማማቸውምና። ዲያብሎስን የሚያሸንፉት መሣሪያቸው በሆነው በትሕትና ነው።

❖ አንድ ጊዜ ቅዱስ መቃርዮስ ብቻውን በበረሃ በሚያልፍበት ጊዜ ዲያብሎስ ፊቱ እጅግ በሚያስፈራና በሚያስጠላ ፍጥረት አምሳል ሆኖ በመንገድ ተገናኘው። እርሱም ቅዱስ መቃርዮስን እንዲህ አለው፡- "አንተ መቃርዮስ ምን ያህል ብርቱ ነህ? ዝናህ ልክ እንደ ርእሰ መነኰሳት አባ እንጦንስ ከምሥራቅ እስከ ደቡብ ድረስ ተሰማ። ኤልሳዕ ኤልያስን እንደ መሰለው አንተም እርሱን መስለኸዋልና።[202] አባ እንጦንስ ራሱ የአንተ አስተማሪ ነው፡ እርሱ አመንኲሶሃልና። በእውነት አንተ በትሕትናህ አብዝተህ ተዋግተኸኛል፡ ምክንያቱም አንተ ይህን እውነተኛውን ትሕትና ከአባ እንጦንስ በፍቅር ሆነህ ተቀብለሃልና። እኔ በብዙ ሕማምና ጸር ብዋጋህም አንተ ግን በዚህ በረሃ ውስጥ ሆነህ ዘወትር ከልብህ በሆነው ጥልቅ እምነትህ ወደ ፊት እየገሰገስክና እየተጋህ አልቻልኩህም" አለው።

---

[202] ፩ኛ ነገ. 19፡19-21

❖ አባ መቃርዮስም "እግዚአብሔር አንተን ስለሚያውቅ ልቤንና አምነቱን አጠነከረልኝ፥ በአንተ ላይም ብርታትን ሰጠኝ። ይህ ከእግዚአብሔር ያገኘሁትና ከአባ እንጦንስ የተማርኩት ሥጋዊ ነገር አይደለም፥ ነገር ግን ጸሎቱ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ባለው እንደ ዕጣን ዘውትር የሚያርግ ፍጹም መንፈሳዊ ነገር ነው እንጂ" አለው። ዲያቢሎስ ይህን ቃል በሰማ ጊዜ እንደ ጢስ ተነነ፥ እርሱም እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሄደ።[203] ዲያብሎስ ሁል ጊዜ ትዕቢተኛ ስለሆነ በእውነት ትሑት የሆነ ሰው ያሸንፈዋል። ለዚህ ነው ቅዱስ መቃርዮስ "ጸም ያለ ጸሎትና ትሕትና አንድ ክንፉ እንደ ተሰበረ ንስር ነው" ያለው።

❖ እንዲሁም ቅዱስ መቃርዮስ በአንድ ወቅት ከአጎው ጋር የዘንባባ ቅጠል ይቆርጥ ዘንድ ማጭድ ይዞ በረሃውን አቋርጠ ሄደ። ያን ጊዜ የያዘውን ማጭድ ቀምተው ይገድሉት ዘንድ ሰይጣናት በእርሱ ላይ በአንድነት ተሰበሰቡ። ወዲያውም አባ መቃርዮስን ለመምታት ሞከሩ፥ ነገር ግን አልቻሉም። አባ መቃርዮስም ልቡ እንደ አንበሳ ጽኑዕ ነበርና በታላቅ ድምፅ በእነርሱ ላይ በመጮኽ "ትመቱኝ ዘንድ ከእግዚአብሔር ተፈቅዶላችሁ ከሆነ ያሰባችሁትን ፈጽሙ፥ አለበለዚያ ግን ከእኔ ዘንድ ውጡ፡ ወደ ጥልቁ ገሀነም ግቡ" አላቸው። ያን ጊዜም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው "መቃራ ሆይ፥ ከአንተ የተነሣ ወዮልን፡ ድካማችንና ግብራችን ሁሉ በአንተ ዘንድ ከንቱ ሆኖብናልና" አሉት።

እነርሱም በአንድ ላይ በመሰባሰብ እየጮኹ ለአባ መቃርዮስ እንዲህ አሉት፡- "መቃርዮስ፥ አንተ በጣም

---

[203] ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ የተጋድሎ ሕይወቱና ትምህርቱ፥ ገጽ 59፡ 72

ኃይለኛ ነህ፡ በአንተ ላይ ምንም ነገር ለመሥራት አልቻልንም፤ እስከ ዛሬ ድረስ አንተን ለማጥቃት በአንተ ላይ የተለያዩ ፈተናዎችን በማምጣት ብዙ ብንደክምም አንድስ እንኳ ረብ ጥቅም አላገኘንም፡፡ ተመልከት፡ ምንም ይሁን ምን ብትሠራ እኛም እንሠራለን፡ አንተ ትጸማለህ፡ እኛ እንዲያውም ከነጭራሹ አንበላም፡ አንተ ሌሊት ከእንቅልፍ ጋር በመጋደል በጸሎት ትተጋለህ፡ እኛ ፈጽሞ አንተኛም፡ በአንድ ነገር ብቻ አንተ ታሸንፈናለህ፡፡" "አባ መቃርዮስም "እርሱ ምንድን ነው?" አለው፡፡ ዲያብሎስም "ትሕትናህ ነው፤ ከትሕትናህ የተነሣ በአንተ ላይ ምንም ነገር ላደርግ አልቻልኩም" አለው፡፡ ቅዱስ መቃርዮስም "ይህን የሚያደርገው የእኔ ኃይል አይደለም፡ በውስጤ ያደረው የእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ" አላቸው፡፡ ያን ጊዜም ከእርሱ ተሰወሩ፡፡[204]

❖ አባ ኤስድሮስም ""የትሕትና ልዕልናና ክብር እጅግ ታላቅ ነው፤ የትዕቢት አወዳደቅ ጥልቀት ደግሞ እጅግ ጥልቅ ነው፡፡ ስለዚህ ትሕትናን እንድትከተል፡ ከትዕቢት ደግሞ እንድትርቅ እመክርሃለሁ" አለ[205]፡፡ አንድ አረጋዊም "በትዕቢት ከሚሆን ድል አድራጊነት ይልቅ በትሕትና የሆነ መሸነፍ ይሻለኛል"[206] አለ፡፡ ሌላ የእግዚአብሔር ሰውም "በአጠገብህ ያለውን ሰው አትናቀው፡ አትንቀፈውም፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው በአንተ ላይ ይሁን ወይም በእርሱ ላይ አይታወቅምና፡፡ በአጠገብህ ያለው ማለቴም አንተን የሚያገለግልህን ሰው ማለቴ ነው"[207] አለ፡፡

---

[204] ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ የተጋድሎ ሕይወቱና ትምህርቱ፡ ገጽ 88
[205] ከበረሓውያን ሕይወትና እንደበት፡ ገጽ 79
[206] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 82
[207] ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 82

Scanned by CamScanner

ጌታችንን ያጠመቀውና መጥምቀ መለኮት የተባለው ቅዱስ ዮሐንስም ስለ ጌታችን ሲናገር፡- "እኔ የሚማውን ጠፍር ለፈታ የማይገባኝ፣ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው"[208] አላቸው። ብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስም "ከሁሉም በኋላ እንደ ሞንጎ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ"[209] አለ።

ስለዚህ ትሑት ሰው ማለት ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት ሁሉ ራሱን ዝቅ በማድረግ "እኔ ምናምንቴ ነኝ፣ አመድ ነኝ፣ ደካማ ነኝ" ብሎ የሚያስብና በማንኛውም ነገር በሚያስፈልገው ቦታ ለሌሎች ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። በሚታመምበትና በሚቆሰልበት ላይ እንኳን ቢሆን የማይቆጣና ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ኃይል ይደግፈዋል፣ ዲያብሎስ ከሚወረውረው ፍላጻም ሁሉ ይጠብቀዋል።

ትሕትና ማለትም በቃል ብቻ ለይስሙላ "እኔ ደካማ ነኝ፣ ኃጢአተኛ ነኝ . . ." እያሉ በልብ ግን ራስን ከሌሎች የተሻለ አድርጎ ማሰብ፣ እኔ እበልጣለሁ ማለትና ለራስ ቦታ መስጠት አይደለም። ሰው በሌላው ላይ የሚቆጣው ራሱን ከወንድሙ በላይ ከፍ አድርጎ ሲቆጥር ነውና። ቅዱስ ዳንኤል ዘጋዛ እንዲህ እንዳለ፡- "ማንም ሰው ሌላውን ወንድሙን ዝቅ አድርጎ ካልተመለከተውና ካልናቀው በስተቀር በማናገረው ነገር አይቆጣበትም፣ እርሱንም አይቆጣውም"[210]

ቃላቱ ቅዱስ እንጦንስ ዲያብሎስ በዓለም ላይ ድንኳኑን ዘርግቶ ባየ ጊዜ "በእግዚአብሔር ፊት ወደቀና አቤቱ፣ ከዚህ የዲያብሎስ ተንኮል ማን ሊያመልጥ ይችላል?" አለ። የእግዚአብሔርም ድምጽ ከሰማይ መጣና "ትሑታን ከእነርሱ ያመልጣሉ" አለው።" ቅዱስ እንጦንስም ሲመክር "ትሕትናን ገንዘብ አድርግ፣

---

[208] ዮሐ 1፡27፣ የሐዋ13፡25
[209] 1ኛ ቆሮ. 15፡8
[210] The Life of Dorotheous of Gaza, Discourses & Sayings, p.253, (No. 17)

Scanned by CamScanner

ምክንያቱም እርሷ እንደ ፍቅር [illegible] ቅዱስ ጳውሎስም "እንግዲህ እንደ [illegible] ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ [illegible] ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ [illegible] ስለዚህ ጌታችን "ያለ እኔ አንዳች [illegible] ፍሬ ሥራችን ጥረት ምንም ማድረግ [illegible] የሆነው እግዚአብሔርን በልግስናው ትሕትናን [illegible] እንዲረዳን መጸለይ ይገባናል፡፡

እማሆይ ቴምድራ እንዲህ አለች፡፡ "ሰውን [illegible] ብሕትውና ወይም ትጋፃ ሌሊት ወይም [illegible] መከራ መቀበል ሳይሆን አውነተኛ ትሕትና [illegible] የሚያባርራቸው አንድ ባሕታዊ ነበር፡፡ እርሱም [illegible] "እንድትወጡ የሚያደርጋችሁ ምንድን ነው? [illegible] "ጾም ነውን?" አላቸው፡፡ እነርሱም "እኛ ፈጽሞም [illegible] አንጠጣም" አሉት፡፡ "ትጋፃ ሌሊት ነውን?" አላቸው፡፡ "እኛ ፈጽሞ አንተኛም" አሉት፡ "ከዓለም መለየት ነውን?" አላቸው፡፡ እነርሱም "እኛ የምንኖረው በበረሓ ነው" አሉት፡፡ "ታዲያ ይኼ ሁሉ እንድትወጡ የማያደርጋችሁ ከሆነ የሚያስፈራችሁና የሚያባርራችሁ ምንድን ነው?" ሲላቸው "እኛን ከአውነተኛ ትሕትና በስተቀር የሚያሸንፈን ነገር የለም" አሉት፡፡ ትሕትና በአጋንንት ላይ ድል አድራጊ እንደ ሆነ ታያላችሁ[illegible]

6.2.3.3. እግዚአብሔር ወደ ትሑታን ይመለከታልና

እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚጠላ ሁሉ ትሑታንን ደግሞ ያፈቅራቸዋል፡ በዓይነ ምሕረቱም ይመለከታቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ወደ ማን እንደሚመለከት በግልጽ ነግሮናል፡ እንዲህ

---

211 ቆላ 3፡12

212 ከበረሓውያን ሕይወትና አንደበት፡ ገጽ 84

ሲል፡- "እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፡ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፡ በቃሌም ወደ ሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ"[213] እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ዋናው ነገር ምን እንደ ሆነም "ሰው ሆይ፡ መልካሙን ነግሮሃል እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፡ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፡ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?"[214] በማለት ነግሮናል፡፡

ሐዋርያውም "ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፡"[215] "በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፡ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ"[216] እያለ ትሕትናን ገንዘብ እናደርግ ዘንድ ደጋግሞ አስተምሮናል፡፡

6.2.3.4.. እግዚአብሔር ትዕቢተኛ ልብ አይወድምና

እግዚአብሔር ትዕቢትንና ትዕቢተኛን ሰው የማይወድ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፊውና በጥልቀት ይነግሩናል፡፡ ለአብነትም የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- "ጐበዞች ሆይ፡ ለሽማግሊዎች ተገዙ፡ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፡ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፡ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"[217]

---

[213] ኢሳ. 66፡2
[214] ሚክ. 6፡8
[215] ፊል. 2፡3
[216] ኤፌ. 4፡2
[217] 1ኛ ጴጥ. 5፡5

- "እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ የትዕቢትን ነገር አታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትቱ።"[218]
- "እናንተ ፍርዱን የጠበቃችሁ የምድር ትሑታን ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ፈልጉ ጽድቅንም ፈልጉ፥ ትሕትናንም ፈልጉ፥ ምናልባት በእግዚአብሔር ቍጣ ቀን ትሰወሩ ይሆናል።" [219]
- "ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት ባለጠግነት፥ ክብር ሕይወትም ነው።"[220]
- "እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ትምህርት ነው፥ ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች።"[221]
- "ሰው ሳይወድቅ በፊት ልቡ ከፍ ከፍ ይላል፥ ትሕትናም ክብረትን ትቀድማለች።"[222]
- "ትሑት ልብ የሥጋ ሕይወት ነው፥ ትንእት ግን አጥንትን ያነቅዛል።"[223]

6.2.4. ትዕግሥት

ትዕግሥት ማለት በሕይወታችን ላይ የሚደርስውን ማንኛውንም ነገር በአኩቴትና በጥበዓት መቀበል ነው። ትዕግሥት በጽናት ወደ ፍጹምነት ለመድረስ የምናደርገው የተጋድሎ ጉዞ ነው። በትዕግሥት ተጋድሎ ውስጥ የመጀመሪያው ክፉን በክፉ አለመመለስ ነው። በዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት

---

[218] ሮሜ 12፥16
[219] ሶፎ. 2፥3
[220] ምሳ. 22፥4
[221] ምሳ. 15፥33
[222] ምሳ 18፥12
[223] ምሳ 14፥30

Scanned by CamScanner